# የቀራንዮ መስቀል ራእይ

# The Vision of

# CALVARY'S CROSS

በ ***ቦቢ ኮነር***

ከጣፋጩ የፀደይ ቀን ትኩረቴን ዞር እንዳደረግሁ ሞቃቱ የፀሐይ ብርሃን ለስለስ ብሎ በመስኮቱ በኩል ወደ ቢሮዬ እየፈሰሰ ነበር። ወንበሬ ላይ ተቀምጬ፥ ትኩረቴን መልሼ ተወልውሎ በሚያብረቀርቀው ዴስክ ላይ ወደ ነበሩት ወደ ተከፈተው መጽሐፍ ቅዱሴ እና አንድ በጣም ንፁህ የሆነ ኖትፓድ (የማስታወሻ ደብተር) ላይ አደረግሁ። ስለ **ክርስቶስ** መስቀል ርዕስ ላይ የስብከት ኖቶችን (ማስታወሻዎችን) በማዘጋጀት ሂደት ላይ ነበርሁ። ከዚህ በፊት በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ፥ አሁን ግን የበለጠ አዲስ ነገር በጥልቀት ሽቼአለሁ። ሊሆን ስላለው ነገር አልተዘጋጀሁም ነበር። ፀጥ ያለው ሁኔታዬ በመሠረታዊ መልኩ ሊቀየር ነው። ወንበሬን ወደ ፊት እየገፋሁ ወደ መጽሐፍ ቅዱሱና ወደ ማስታወሻ ደብተሬ ወረቀት እየተጠጋሁ፥ የመስቀሉን መልእክት እውን እንዲያደርግ **የእግዚአብሔርን መንፈስ** እየጠየቅሁ መጸለይ ጀመርሁ። ብዙ ቃላትን ብቻ መጠቀም አልፈለግሁም። መስቀሉ ከመልእክት በላይ እንዲሆን ፈልጌአለሁ። ሰዎች የሕይወትን ቃላት እንዲሰሙ ጓጉቼአለሁ (ሽቼአለሁ)። **የሕይወት ቃል** ህይወታችንን የሚለውጥ ኃይለኛ እንዲሆን ፈልጌአለሁ።

ስለዚህ ጸሎቴን ከተራበ ልብ ጀመርሁ።

በድንገት ያለማስጠንቀቂያ፥ ከብርሃን ፍጥነት በፈጠነ ሁኔታ፥ በጥናቴ ላይ / በቤቴ ቢሮ በምቾት መቀመጤን አልቀጠልሁም ነበር። በ**እግዚአብሔር መንፈስ** በጊዜና በቦታ ውስጥ እየተወሰድሁ ነበር። ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደጠቀሰው፥ **በሥጋ እንደሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደሆነ አላውቅም**። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ በተጨናነቁ **የኢየሩሳሌም** ጎዳናዎች ወርጄ ነበርሁ። የሚረብሽ ሕዝብ ድምፆችን መስማት ችዬ ነበር፥ መንፈሴን በጣም እንዳይመቸው ያደረገ በአየር ውስጥ አንድ ክፉ ሽብር መስማት እችል ነበር። እኔ በታላቅ የሕዝብ ጭንቅንቅ ውስጥ ቆሜ ነበር። ፊታቸውን ስመለከት፥ አንዳንዶች በሐዘን ተሞልተው እንደነበር እና ሌሎች በክፉ ፈገግታ ተሞልተው እንደነበር ልብ አልሁ። የማውቀው ቀጣዩ ነገር "*ከመንገዱ ተወገድ!*" በማለት በረገመኝና በጮኸብኝ በአንድ ትልቅ ሮማዊ ወታደር ወደ ጎን መገፍተሬን ነበር። ከዛ የተጨናነቀው ሕዝብ እየጠበቀው የነበረውን ተመለከትሁና አየሁ…**ኢየሱስ** የእርሱን መስቀል ተሸክሞ። ዓይኖቼን ላምን አልቻልሁም። እንዲህ ዓይነት አስከፊ እይታ በፍጹም አይቼ አላውቅም። መንስኤው የእሾሆች አክሊል ከሆነው ቁሥሉ በፈሰሰው ደሙ የ**እርሱ** መላው ፊት በረጋ በደረቀ **ደም** ተሸፍኖ ነበር፥ የእሾኾቹ አክሊል እንደ ሾሉ ምላጭማ ትላልቅ ምስማሮች ራሱ ውስጥ ዘልቀው እንደገቡ ዓይነት በጣም ይመስላል። በእያንዳንዱ ጊዜ የእርሱ ልብ ሲመታ፥ ትኩስ ጠቆር ያለ ሰማያዊ ደም (fresh dark blue-re blood) በምስማሮቹና በእሾኾቹ መሐል ወዲያውኑ ተወርውሮ፥ በግንባሩ ወደ ታች በፍጥነት በመፍሰስ ወደ ዓይኖቹ ውስጥ ይገባ፥ ወደ ደረቱ ይንጠባጠብና በአቧራማው ጎዳና ላይ ይንጠባጠብ ነበር። አእምሮዬ ተሽከረከረ። "*ይህ ሊሆን አይችልም፥ ይህ ከዓመታት በፊት ነው የሆነው።*" በማለት አሰብሁ። በዛ ቅጽበት ዓይኖቻችን ተገጣጠሙ፥ ነገር ግን፥ እኔም ያለጥርጥር ይህ እውን እንደነበረ አወቅሁ። እንደምንም (Somehow)፥ ወደ ስቅላቱ ተወሰድሁ!

ሕልም አልነበረም፤ እኔ እዛ ነበርሁ።

ደንግጬ፥ ከተጨናነቀው ሕዝብ ጋር ተዳዝሁ፥ **ኢየሱስ** ከከባዱ መስቀል ክብደት በታች ሲደናቀፍ ስመለከት ለመናገር በጣም ደንግጬ ነበር። ሞቃት ነፋሶች ከመንገዱ ላይ አቧራ እያነፈሱ በደም በራሱት ልብሶቹ ላይ እንባዎችን ቀላቀሉ እና እኔ የ**እርሱን** የጀርባውንና የትከሻዎቹን ቁሥሎች መልከት አደረግሁ፥ ጥልቅ…ሥጋው-ተቆራርጦ…በስፋት ተከፍቶ…ተከፍቶ (deep…flesh-torn…gaping..open) ነበር። ለረጅም ጊዜ ጉዞአችንን ከከተማዋ ግድግዳ ውጭ ቀጥ ባለ የተራራ ዳገት መንገድ ላይ አደረግን። ከረጅም ጊዜ በኋላ በስተመጨረሻ ወደ የራስ ቅል ስፍራ ወደ ተራራው አናት ላይ መጣን። **ጌታ** በሃይል ወደ ታች ወደ መሬት ሲወረወር የተጨናነቀው ሕዝብ በሽብር አወከ (stirred with excitement)። **እርሱ** ያለትግል ክንዶቹን ዘረጋ።

አየሩ ራሱ በሚጨቁኑ በሰይጣን መናፍስት በጣም ከብዶ ስለነበር ለመተንፈስ ከባድ ነበር። የደም እና የአካል ፈሳሾች ሽታ በጣም ጠንካራ ስለነበረ ታፍኜ ነበረ፤ እና ከወታደሮቹ ከሚመጣ የሆነ ዓይነት አስካሪ መጠጥ፣ ወይም ርካሽ መጠጥ በጠንካራው የሚገማ ሽታ ማሽተት ችዬ ነበር። መዶሻው ምስማሮቹን ሲመታ ምስማሮቹም በእጆቹና በእግሮቹ ውስጥ ዘልቀው ሲገቡ ከባድ ድምፅ ሰማሁ። መስቀሉ በጣም በሀይል ቃል ወደ ላይ ከፍ አለ እና ቀዳዳው (የመሬቱ ቀዳዳ) ውስጥ ገባ። የአካሉ ክብደት በምስማሮቹ ላይ ሲመጣ፥ ከጌታ ጉሮሮ ውስጥ የሚወጣ አንድ ጥልቅ መቃተት ሰማሁ። የዚህን ጊዜ ድምፆች፣ ዕይታዎች፣ እና ሽታዎች በምፁም አልረሳም። ሰዓት እንደቆመ ይመስል ነበር። ምን ያህል ጊዜ እዛ እንደነበርሁ እኔ አላውቅም፤ ለሰዓታት እዛ የሆንሁ ይመስላል።

ይህ ምንም ምሕረት የሌለበት ቦታ ነበር! ሆኖም ከሁሉም በላይ እጅግ መሐሪው ድርጊት እየተፈጸመ ነበር። የስሜቶችን ተጻራሪነት (paradox) በፍፁም አልረሳም። ኃጢአት የሌለበት እና ጥፋት የሌለበት እንደ አንድ ጥፋተኛ እየሞተ። (The Sinless and Guiltless dying as one guilty.) ፍፁሙ በጦር ተወጋ እና በመስቀል በከባዱ ተጎዳ (ravaged)። ጻድቁ ለአመጸኞች እየሞተ። **ክርስቶስ**ን በመስቀል ላይ ለማየት ዓይኖቼን ሳነሣ፥ በፊቱ ላይ ያለው ሥቃይ ልቤ መሸከም ከሚችለው በላይ ነበረ፤ ሁሉም ጥንካሬ እግሮቼን ትቶ ሄደ፥ አካሌ መሬቱ ላይ ሲወድቅም ከባድ ድምፅ ተሰማኝ። በጉልበቶቼ ለመንበርከክ ታገልሁ። ዓይኖቼን አንሥቼ፥ **በጉን** ለማየት ራሴን በድጋሜ ገፋሁ። "**ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም**" የሚለውን የነቢዩን ቃላት አሁን አወቅሁ፥ (ትንቢተ ኢሳይያስ 53፥2)። ካየኋቸው ሁሉ የእርሱ ፊት የበለጠ ደም ግባት አልባ (የበለጠ የጠፋ / more disfigured) እንደነበረ መመስከር እችላለሁ። **ኢየሱስ** የሄደበት (የተቀበለው) ሥቃይ ከመስቀል እጅግ በላይ ነው። ማንኛውም የሰው ቋንቋ ከሚያብራራው እጅግ በላይ ነው። እንደ እኔ ላሉ ኃጢአተኞች ከ**እግዚአብሔር** ጋር የማስታረቅን ሥራ በሞቱ እያደረገ (making atonement for sinners such as I) በምድርና በሰማይ መሐል እንደተሰቀለ የእርሱ ሥጋ የገረጣ ሰማያዊ ነበር። በዛ ጊዜ እንዴት አስከፊ ኃጢአተኛ እንደነበርሁ ማወቄን ለማብራራት መጀመር አልቻልሁም። የመዝሙሩ ቃላት በሙላት ወደ ልቤ ውስጥ መጡ። "**የክብር ጌታ** የሞተበትን አስደናቂ መስቀል በጥንቃቄ ስመለከት፥ በታላቁ የማገኛቸውን ቆጠርሁ ነገር ግን በትእቢቴ ሁሉ ላይ ጥፋትና ንቀት ፈሰሰ።" **ጌታ** ከመስቀሉ ሥቃይ ስር ሲታገል ማየት እችል ነበር፥ **እርሱም** ክብደቱን ከፍ አደረገና እነዚህን ቃላት ለመናገር ወደ ውስጥ ተነፈሰ፥ "**አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው**" (**የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ** መሪነት ደቀ መዝሙሩ ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው 23፥34)።

በኋላ፥ ከሁሉም በላይ እጅግ አሰቃቂ ጩኸት(ለቅሶ) **ከጌታችን** ደርቀው ከተሰነጣጠቁት፣ ካበጡት፣ እየደሙ ካሉት ከንፈሮች ወጣ…ይህ ጩኸት በአሁኗ ሰዓትም በጆሮዬ ውስጥ አሁንም ያቃጭላል:- "**ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ?** (**አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?**)" (**የእግዚአብሔር አብ ልጅ እና ቃል የጌታችንና**

**የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ** *መሪነት ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ እንደጻፈው* 27፥46)።

*ይህ ጥያቄ* **ከእግዚአብሔር ልጅ** ከራሱ ነፍስ *መጣ*። በዘላለም ውስጥ ሁሉ *ለመጀመሪያ ጊዜ*፥ **ልጅ** እና **አባት** *ተለያዩ* (For the very first time in all of eternity, **the Son** and **the Father** are separated.)። **ክርስቶስ እግዚአብሔርን አባት** ከማለት ሌላ **አምላክ** ብሎ የጠቀመው በጣም የመጀመሪያው ጊዜ *ነው* (This is the very first time **Christ** has ever referred to **God** other than **Father**.)። ለምን? ምክንያቱም አሁን **ክርስቶስ** እኛ የሆንነውን ሆነ፥ እርሱ የእኛን ኃጢአት ወስዶ በራሱ ላይ አደረገ። **እግዚአብሔር** የላቀ እጅግ ንጹሕ የሆነ ዓይን ስላለው ኃጢአትን ለመመልከት ራሱን አያሰናዳም በማለት *መጽሐፍ ቅዱስ* ይጠቅሳል፥ ስለዚህ **እግዚአብሔር አብ** የራሱ **ልጅ** ላይ ጀርባውን አዞረበት፥ **ክርስቶስም በአባቱ** *ተተወ* (The Scripture states that **God** is of a purer eye than to look upon sin, so **Father God** turns His back to **His Son**, and **Christ** is forsaken of **His Father**.)። በአትክልት ስፍራው ውስጥ "**ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ**" በማለት ሲጸልይ ሳለ ከእርሱ እንዲወሰድ (እንዲወገድ) የጠየቀው *ሥቃይ ይህ ነው* (**የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ** *መሪነት ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ እንደጻፈው* 26፥39)። **እርሱ** ራሱ በአባቱ መተዉን ማሰብን መሸከም አይችልም። በዚህ ጊዜ **ክርስቶስ** እንደ አንድ ልጅ አይደለም እየሞተ ያለው፥ ይልቅ ግን እንደ አንድ ኃጢአተኛ። ይህ ሲሆን፥ የእርሱ ልብ ተሰብሮ ነበረ። *መዝሙረኛው* እንደተነበየው:- "**ልቤ እንደ ሰም ቀለጠ፥ በአንጀቴም መካከል ቀለጠ**" ("**My heart is like wax, it has melted within Me**") (*መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር* 22፥14)።

ከዛ **ክርስቶስ ኢየሱስ** በታላቅ ድምፅ ጮኾ:- "**አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ**" አለ (**የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ** *መሪነት ደቀ መዝሙሩ ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው* ምዕራፍ 23፥46)፥ እናም የሞተው ራሱ ተዝለፍልፎ በደረቱ ላይ *ተጋደመ* (and His lifeless head falls limp upon His chest.)። *መላው ምድር* እየተሽከረከረና እየተንቀጠቀጠ ነበረ፤ የሆነ ኃይለኛ ጨለማ በሁሉም ቦታ ነበረ። ከጨለማው ውስጥ ጩኸቶች ሲመጡ እሰማለሁ፥ በድንገትም ጩኸቱ የመጣው ከራሴው ከንፈሮች እንደሆነ አወቅሁ። ከዚያ ወዲያ በመስቀሉ እግርጌ አይደለሁም፥ ተመልሼ ቢሮዬ ውስጥ ነኝ፤ ነገር ግን ለቅሶውና ጩኸቱ አሁንም በጆሮዎቼ ውስጥ ያስተጋባል። መላው አካሌ እየተንቀጠቀጠና እየተንቀጠቀጠ (እየተወዛወዘ) ነው።።

*(ራእዩ ተፈጸመ)*

## RITUAL OR RELATIONSHIP (*ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርአት ወይስ ኅብረት*)

በዚህ ጊዜ ላይ ያየሁትንና የተለማመድሁትን ሁሉ ለማካፈል አልችልም፥ ነገር ግን በፍፁም ያው እንደማልሆን ልነግራችሁ እችላለሁ። እኔም ከቀድሞው ይልቅ አሁን የበለጠ እርግጠኛ ነኝ፥ **የመስቀሉ ቃል ለመዳን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።** *መጽሐፍ ቅዱስ* እንዲህ ይናገራል:- "**ለማጥመቅ ክርስቶስ አላከኝምና፥ ወንጌልን ልሰብክ እንጂ፤ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም።**" (1ኛ። *ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች* 1፥17)።
**የክርስቶስ መስቀል** በአንገታችን ላይ የሚደረግ ተራ ጥቃቅን ጌጣጌጥ ወይም የሆነ ቡቡ(sentimental) የበዓል ጌጥ አይደለም፤ ይልቅ ግን መስቀሉ ወደ ወደቀው የሰው ዘር የደረሰ **የእግዚአብሔር አብ አፍቃሪ ልብ** እውን ባህርይ (essence) *ነው*። የሰው ዘር ከኃጢአት መያዝና ጥፋተኝነት የሚድንበት ብቸኛ ተስፋ በመስቀል ላይ የተፈጸመው **የክርስቶስ** ***ሥራ*** *ነው*። **እግዚአብሔር** ሰውን ዝም ብሎ ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት እንዲይዝ እየጠየቀው አይደለም፥ ይልቅ ግን ዘለቄታዊ ወደ ሆነ ኅብረት እንዲገባ እየጠየቀው ነው (**God** is not

requesting man to embrace a mere ritual, but rather to enter into a lasting relationship.)። **በክርስቶስ** መስቀል ብቻ ነው ይህ መፈፀም የሚችለው።

## THE CROSS WAS BY DIVINE DESIGN (መስቀሉ በመለኮታዊ እቅድ/አሠራር ነበረ)

ወንጌል ይህ ነው "**መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፥**" (1ኛ። ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 15፥3-4)። "**መጽሐፍም እንደሚል**" የሚለውን ቃል ልብ በሉ። ለኃጢአታችን በመስቀል ላይ **የክርስቶስ መሥዋዕት** በመለኮታዊ እቅድ (by divine design) ነበረ። በመስቀል ላይ የክርስቶስ ሞት ያልታሰበ(ድንገተኛ) አይደለም አጋጣሚም አይደለም (The death of **Christ** upon the cross was neither accidental nor arbitrary.)። **ኢየሱስ**:- "**እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤**" በማለት ገልፆአል። **ጌታ ኢየሱስ** ከሞቱ አስቀድሞ ስለ መስቀሉ እንደተናገረ ወንጌል ይነግረናል (**የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ** መሪነት ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ እንደጻፈው 10፥38፤ **በመንፈስ ቅዱስ** መሪነት ደቀ መዝሙሩ ቅዱስ ማርቆስ እንደጻፈው 10፥21፤ **በመንፈስ ቅዱስ** መሪነት ደቀ መዝሙሩ ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው 14፥27)።

ለኃጢአተኛ የሰው ዘር በመስቀል ላይ **የክርስቶስ** መሥዋዕት **የእግዚአብሔር ፍቅር** እጅግ ታላቁ ምሳሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "**ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።**" በማለት ገልፆአል (**የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ** መሪነት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንደጻፈው 15፥13)። **ኢየሱስ** ለእኛ ያደረገልን በትክክል ያን ነው። **እርሱ** የራሱን ሕይወት ቤዛ አድርጎ በመስጠት የወደቀውን ሰው ለማዳን በፈቃደኝነት ወደ ዓለም መጣ። ጳውሎስ እንዲህ አለ:- "**ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። ...ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።**" (ወደ ሮሜ ሰዎች 5፥6-8)። ጥፋተኞቹ እኛ ነን እና የ**እግዚአብሔር** ፍርድ ይገባናል፥ ነገር ግን **እግዚአብሔር** እንዲሁ ስለወደደን የራሱ **ልጅ** ለእኛ ኃጢአት እንዲሆን ለመፍቀድ ፈቃደኛ ነበረ፥ ስለዚህ እኛ **እርሱን(የእግዚአብሔር ልጅን)** እንደ ግላችን **ጌታ** እና **አዳኝ** አድርገን በመቀበል ከኃጢአት ቅጣት ነጻ መሆን እንችላለን።

በአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ውስጥ **ክርስቶስ በሞቱ** የኃጢአተኛን ቦታ እንደወሰደ መቅረቡን ማንም ሳያይ መቅረት አይችልም (None can fail to see that in the teaching of the New Testament, Christ is set forth as taking the place of the sinner in His death.)። በቀራንዮ መስቀል ላይ **የኢየሱስ ሞት** የወኪልነት ነበረ፥ ማለትም የእኛን የሞትና ቅጣት ቦታ **ክርስቶስ** ወሰደ። እያንዳንዱ የድኅነት በረከት **በክርስቶስ ሞት** አማካኝነት ለአማኝ ተሰጥቶአል (Every blessing of salvation is imputed to the believer by the substitutionary **death of Christ**.)። "**እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።**" (2ኛ። ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5፥21)

መስቀሉ፣ እና የመስቀሉ ቃል የክርስትና እጅግ ዋናውና መሐሉ ነው (The cross, and the preaching of the cross, is the very core, and center of Christianity.)። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- "**እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።**" (**የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ እውነት ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ** መሪነት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንደጻፈው 12፥32)። የሚለውጠውን **የክርስቶስን መስቀል** መልእክት በድፍረት ለማወጅ **እግዚአብሔር**:ይርዳን።

በ ቦቢ ኮነር
by Bobby Conner

**የእሥራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ የእግዚአብሔር አብ ቃልና ልጅ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ቅዱስ እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** የልጁን የቶማስ ቶሙክዳህታን አካል ተጠቅሞ ተረጎመው። hithomasgetachew@gmail.com። ክብር፥ ኃይል፥ ባለጠግነት፥ ጥበብ፥ ውዳሴ፥ ቅድስና፥ ንግሥና፥ አምልኮ ሁሉ በሦስተኛው ቀን ከሞት ለተነሣው፥ **በእግዚአብሔር አብም ቀኝ በክብር ላለው፥ ሥልጣን ሁሉ በሰማይም በምድርም የእርሱ ለሆነ፥ እጅግ በቅርቡም ዳግም መጥቶ ልጆቹን በመንጠቅ ወደ ቅዱስ መንግሥቱ ለሚወስደው፥** ለጌታችንና ለመድኃኒታችን **የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን። ሃሌ ሉያ፥ **ጌታ ኢየሱስ መሢሑ** አሜን።